



# ሀገር አቀፍ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የግንዛቤና የህዝብ ንቅናቄ ሰነድ

ከጥር 22-ግንቦት 07/2009ዓ.ም



በብሔራዊ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ የቀረ

አዲስ አበባ

ታህሳስ 2009 ዓ.ም

# ማውጫ


| ተ.ቁ | | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | የእቅዱ መነሻና ነባራዊሁኔታ | 1 |
| | 1.1. የመንገድ ትራፊክ አደጋ በዓለም አቀፍ ደረጃ | 1 |
| | 1.2. በኢትዮጵያ የመንገድ ትራፊክ ደንነት ያለበት ሁኔታ | 3 |
| 2. | የሀገራዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ ዓላማ | 5 |
| 3. | የሀገራዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ ግብ | 5 |
| 4. | የንቅናቄ መደረኩ መሪ ቃል | 5 |
| 5. | ከንቅናቄ ፕሮግራሙ የሚጠበቅ ውጤት | 5 |
| 6. | የእቅዱ አፈፃፀም ወሰን | 6 |
| 7. | የንቅናቄ ፕሮግራሙ ከመካሄዱ በፊት የሚከናወኑ ተግባራት | 6 |
| | 7.1. በእቅዱ አተገባበር ዙሪያ ግንዛቤ መፈጠር | 6 |
| | 7.2. የህትመት ስራን በተመለከተ | 7 |
| | 7.3. የዶክመንተሪ ፊልም ዝግጅትን .በተመለከተ | 7 |
| | 7.4. የስልጠና ማኑዋል ዝግጅትን በተመለከተ | 8 |
| | 7.5 .የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት | 9 |
| | 7.6. መንገዶችን ለመንገድ ተጠቃሚዎች ምቹ የማደረግ ስራ | 10 |
| | 7.7. የትራፊክ ህጎች ትግበራ ላይ ቁጥጥር ማድረግ | 10 |
| | 7.8. የአሽከርካሪ ብቃት ህጋዊነትን የማረጋገጥ ስራን ማከናወን | 11 |
| | 7.9. የጥያቄና መልስ ውድድር ማካሄድ | 11 |
| | 7.10 የፓናል ውይይት ማካሄድ | 11 |
| | | 11 |
| 8. | ንቅናቄ በየደረጃው የሚተገበርበት የአፈፃፀም አቅጣጫ አደረጃጀት | 11 |
| 9. | የንቅናቄ መድረኩ አተገባበር | 13 |
| 10. | በክልሉ/በከተማ መስተዳድሩ/የንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ የሚተገበርበት አግባብ | 15 |
| 11. | በፌደራል ደረጃ እቅዱን ተግባሪያዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ አደረጃጀት | 16 |
| | 11.1. ብሔራዊ ኮሚቴ | 16 |
| | 11.2. አብይ ኮሚቴ | 18 |
| | 11.3.የክልሉ (የከተማው)አብያ ኮሜቴ | 20 |
| | 11.4 ንዑሳን ኮሚቴ | 22 |
| | 11.4.1. የህዝብ ግንኙነት፣ቅስቀሳና መስተንግዶ/ሚዲያ/ ንዑስ ኮሚቴ | 22 |
| | 11.4.2. የህትመትና ኤግዚቢሽን ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ | 24 |
| | 11.4.3. የሎጂስቲክ ንዑስ ኮሚቴ | 25 |
| | 11.4.4. የግንዛቤና ስልጠና ዝግጅት ኮሚቴ | 26 |

11.4.5. ስፖንሰር አፈላላጊ ንዑስ ኮሚቴ........................................ 27
11.4.6. የዶክመንተሪ ፊልም ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ............................ 28

12. የንቅናቄ ፕሮግራሙ አተገባበር የክትትልና ድጋፍ አግባብ.................... 29
13. የፋይናንስ ፍላጎት በፌደራል ደረጃ ............................................. 29
14. በእቅድ ትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች........................ 29
15. ሊወሰድ የሚገባው መፍትሄ....................................................... 30
16. ማጠቃለያ ........................................................................ 30
17. የድርጊት መርሃግብር............................................................. 31

## መግቢያ

# 1. የእቅዱ መነሻና ነባራዊ ሁኔታ


## 1.1 የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዓለም አቀፋዊ ገጽታዎች

በአሁኑ ወቅት አለማችንን ክፉኛ እያሳሰቧት ከሚገኙ ገዳይ ሠው ሠራሽና የተፈጥሮ በሽታዎች ውስጥ የመንገድ ትራፊክ አደጋ አንዱ ሆኖ ይገኛል፡፡ ትንሽ ጥንቃቄ በማድረግ በቀላሉ ሊከላከሉት በሚችሉት በዚህ አደጋ ሳቢያም የብዙ ሰዎች ደጃፍ እየተዘጋ፣ ቤተሠብ እየተበተነ፣ ለአካል ጉዳት እየዳረገ ፤ንብረት እየወደመና ሀገራትም ከድህነት ለመላቀቅ የሚያደርጉትን ጥረት እየጐተተ ይገኛል፡፡

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት 2015 ሪፖርት በዓለማችን በዓመት ከ1.24 ሚሊዮን በላይ ሠዎች በመንገድ ላይ ሆነው አልያም በትራንስፖርት ከቦታ ወደቦታ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት ባላሠቡትና ባልጠበቁት ሁኔታ ህይወታቸውን ያጡ ሲሆን ከ20-50 ሚሊዬን የሚደረሱት ደግሞ ለከባድና ቀላል የአካል ጉዳት እየተዳረጉ እንደሚገኝ ያረጋገጣል፡፡ አደጋው ዝቅተኛና መሀከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች በጣም የከፋ ከመሆኑም በላይ እነዚህ ሀገሮች ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች ከሚደርስባቸው የሞት አደጋ እጥፍ የሚደርስባቸው ሲሆን በአለም ላይ ከሚደርሰው ሞት አደጋ 90% በነዚህ ዝቅተኛና መሀከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች የሚድረስ መሆኑንም መረጃው ያመላክታል፡፡ በተለይም አፍሪካ ካለት በጣም ዝቅተኛ ከሆነ የተሽከርካሪ ቁጥር አኳያ የሚመዘገብባት የአደጋ መጠን እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ እንደሚገኝ የአለም ጤና ድርጅት ሪፖርት

ያሰገነዝባል ። የመንገድ ትራፊክ አደጋ በአሁን ሰዓት በአለም ላይ አጠቃላይ ገዳይ ከሚባሉት በሽታዎች ውስጥ በ9ኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ከቀጠለ በ2030 ወደ 3ኛ ከፍ እንደሚል ይጠበቃል፡፡

የአለም ጤና ድርጅት በ2015 ይፋ በደረገው በዚሁ መረጃ መሰረት እድሜያቸው ከ15-29 አመት ክልል ውስጥ ያሉ ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝ የሆኑ ወጣቶችን በመግደል ቀዳሚ ከሆኑ 10 በሽታዎች ውስጥ የመንገድ ትራፊክ አደጋ የአንደኝነት ደረጃን ይዞ እናገኘዋለን፡፡




ምንጭ:-የዓለም ጤና ደርጅት 2015 ሪፖርት

## 1.2 በኢትዮጵያ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ያለበት ሁኔታ

በሀገራችን የገቢና የወጪ እቃዎች ዝውውር 90% እንዲሁም ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ክንውኖች ከሚደረገው የመንገደኞች እንቅስቃሴ 95% ያህሉ አገልግሎት የሚያገኘው በመንገድ ትራንስፖርት አማካይነት ነው፡፡

በመሆኑም ይህ ዘርፍ ለሀገር ልማትና እድገት የጀርባ አጥንት በመሆን እያበረከተ ካለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦ አንጻር ዘርፉ በተገቢና በተጠናከረ እንዲሁም በተቀናጀ ሁኔታ ካልተመራ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ሊያመዝን እንደሚችል አያጠራጥርም፡፡

በአሁኑ ወቅት መንግስት ለመሠረተ ልማት አውታር ዝርጋታዎችና ለግል ባለሀብቶች በፈጠረው ምቹ ሁኔታና በሀገሪቱ እየታየ ካለው የኢኮኖሚ መነቃቃት ጋር በተያያዘ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ይገኛል፡፡ ይህ ሁኔታም የዜጐችን ከቦታ ወደ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመስራት፣ የማደግና የመለወጥ ፍላጐትን ጨምሯል፡፡ ከዚሁ የዜጐች እንቅስቃሴና የተሽከርካሪዎች ዝውውር ጋር በተቆራኘ የትራንስፖርት አገልግሎቱ በተጠናከረ የቁጥጥር ስራ ተደግፎ ባለመመራቱ በፍጥነት፣ በግለኝነትና በቸልተኝነት ምክንያት በርካታ የመንገድ ትራፊክ አደጋ እየተከሠተ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

የአደጋው ተጎጂዎች በአመዛኙ ለሀገሪቱ ወሳኝ የሆኑ ወጣቶች እንዲሁም የተማሩና አምራች የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መሆናቸው ሲታሰብ ደግሞ እንደ ሀገር እየደረሰ ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ቀላል አለመሆኑን መገመት አያዳግትም፡፡

በዓለም አቀፍ የመንገድ ትራፊክ አደጋ መመዘኛና መለኪያ ሆኖ እየተሰራበት ባለው በ10,000 ተሽከርካሪዎች የሞት አደጋ ሲሰላ በሀገራችን በ2008 በጀት ዓመት 61.4 የሰው ሞት ሲደርስ በመንገድ ትራፊክ አደጋ መከላከል ዙሪያ ከፍተኛ ሥራ በሰሩ ሀገሮች ይህ አሃዝ ከ 10 በታች ሲሆን በአፍሪካም ከ30 በታች ይመዘገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ሀገራችን በመንገድ ትራፊክ አደጋ በከፍተኛ ደረጃ ካሉት ተርታ እንድትሰለፍና እንድትታወቅ አድርጓታል፡፡

ይህንን አሳሳቢ የመንገድ ትራፊክ አደጋ ለመቀነስ በተባበሩት መንግስታት ድረጅት የ10 ዓመት የተግባር ዕቅድ (እ.ኤአ ከ2011-2020) የተዘጋጀ ሲሆን ሀገራችንም የተባበሩት መንግስታት ባደረገው ጥሪ መሠረት የመንገድ ደህንነት የተግባር 10 ዓመት ዕቅድ ከ2004- 2013 ዓ.ም ባለው 10 ዓመት ውስጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ተጀምራል፡፡

በሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ላይ (2012 ዓ.ም) አሁን በየ10,000 ተሽከርካሪዎች በትራፊክ አደጋ ምክንያት በሰው ላይ የሚደርሰው ሞት ወደ 27 ዝቅ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡

መንግስትም ለጉዳዩ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን በተለይም የተለያዩ የአሰራር ስርዓቶችን የመዘረጋት፣የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን የማሻሻልና የማዘጋጀት እንዲሁም ዘረፉ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን የማድረግና ሌሎችንም ስራዎች በማከናወን ላይ የሚገኝ በመሆኑ የመንገድ ትራፊክ አደጋው መንግስትና ህዝብ የሚጠብቁትን ያህል ባይሆንም የመቀነስ አዝማሚያ ሊያሳይ ችሏል።

## 2. የፕሮግራሙ ዓላማ:-

- የመንገድ ትራፊክ አደጋ በሰው ህይወትና አካል እንዲሁም ንብረት ላይ እያስከተለ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል ህዝባዊ ንቅናቄ መፍጠር፤

## 3. የፕሮግራሙ ግብ:-

- በግንዛቤ የዳበረና የኔነት ስሜቱ የጎለበተ ማህበረሰብን በመፍጠር በመንገድ ተጠቃሚዎች ስህተት ምክንያት የሚደርሱ የመንገድ ትራፊክ አደጋዎችን መቀነስ፤

## 4. የንቅናቄ ፕሮግራሙ መሪ ቃል:–

- ከትራፊክ አደጋ የፀዳ የትራንስፖርት አገልግሎት ለህገራዊ ህዳሴ !

## 5. ከንቅናቄ ፕሮግራሙ የሚጠቅ ውጤት

- ግንዛብው ያደገና የባለቤትነት ስሜቱ የጎለበተ የመንገድ ተጠቃሚ ይፈጠራል፡፡
- አደጋውን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ያደገ የህዝብ ተሳትፎ ይኖራል፡፡
- አደጋውን በመከላከል ሂደት ውስጥ በየደረጃው የሚገኘው የመንግስት ከፍተኛ አመራር ተሳተፎ የላቀ ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡
- ችግሩን ለመፍታት ጠንክረው የሚንቀሳቀሱ የህይማኖት ተቋማት ይበረክታሉ፡፡
- አደጋውን ለመቀነስ በሚደረገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የህዝብ አደረጃጀቶች ሚና የጎላ ይሆናል፡፡
- አደጋን ተከላከሎ ማሽከርከር የሚችልና ሃላፊነት የሚሰማው አሽከርካሪ ቁጥር ይጨምራል፡፡

- የኪነጥበብ ባለሙያዎች ተሳተፎ ያድጋል፤ኪነጥበባዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት መልዕክት በስፋት ይሰራጫል፣

## 6. የንቅናቄ ፕሮግራሙ ወሰን

- ይህ ሀገራዊ ንቅናቄ በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ከጥር 22 ጀምሮ እስከ ሚያዚያ 30/09 ዓ.ም ተግባራያዊ የሚደረግ ይሆናል።
- የበዓሉ ማጠቃለያ የግንቦት ወር የመጀመሪያው እሁድ 2009 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ የሚተገበር ይሆናል።

## 7. በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ከንቅናቄ መደረኩ ትግበራ በፊት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

### 7.1.የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ንቅናቄ አላማና አተገባበር ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር

- በሀዝባዊው የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ንቅናቄ አላማና አተገባበር ዙሪያ እንዲሁም በወቅታዊው የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ነባራዊ ሁኔታ ላይ በማተኮር የክልልና የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ /ባለስልጣን ኃላፊዎችና የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነሮች በተገኙበት በክቡር ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ውይይት ይደረጋል።
- ለዚህ ስራ የተዘጋጀው ሃገራዊ እቅድ ቀርቦ ውይይት ይደረግበታል።

### 7.2 የህትመት ስራን በተመለከተ በክልል ደረጃ

- ➢ የተለያዩ ብሮሸሮች ይዘት ቀረቦ ይገመገማል።
- ➢ የተለዩ ብሮሸሮች ዝግጅትና ህትመት **ብዛት**
  - ✓ ለትራፊክ አደጋ ተጎጂዎች የሚያሰራጩት ብሮሸር ብዛት .........
  - ✓ ለሰልጣኝ አሽከርካሪዎች የሚሰራጭ ብሮሸር ብዛት .........
  - ✓ ተሽከርካሪ ላይ የሚለጠፍ እስቲከር ብዛት ..........
  - ✓ ለሰልጣኞች የሚሰጥ ሰረተፊኬት ብዛት .........
  - ✓ ለእስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች የሚሰጥ የእውቅና ሰርተፊኬት ብዛት .........
  - ✓ የፕሮግራም ማድመቂያ ባነር ብዛት .........
  - ✓ የፖስተር ዝግጅትና ህትመት .........
  - ✓ ለኤግዚቢሽን የሚሆኑ ፎቶዎች ህትመት .........
  - ✓ ለማጠቃለያ ፕሮግራሙ ታዳሚዎች የሚሰራጭ የመ/ት/ደ መልዕክት የተቀረፀበት እስካርብ ብዛት ........
  - ✓ የማጠቃለያ ፕሮግራሙ የጥሪ ወረቀት ዝግጅትና ህትመት ብዛት .........

***ክልሎች እንደክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የተለያዩ የህትመት ስራዎች ያከናውናሉ፣***

### 7.3. የዶክመንተሪ ፊልም ዝግጅት ስራን በተመለከተ በፌደራል ደረጃ

- ➢ የዶክመንተሪ ፊልም ስክሪፕት ተዘጋጅቶ ይገመገማል።
- ➢ ለስልጠና የሚሆኑ የዶከመንተሪ ፊልም ዝግጅት ብዛት 1
- ➢ ህዝባዊ ንቅናቄው ሲተገበር የሚቀርብ አጭር የዶክመንተሪ ፊልም ዝግጅት ብዛት 1

ክልሎች በፌደራል ደረጃ የሚዘጋጁ ዶክመንተሪ ፊልሞችን አልያም እንደክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ ዶክመንተሪ ፊልም በማስራት የሚያሰለጥኑ ይሆናል፡፡

## 7.4. የስልጠና ማኑዋል ዝግጅትን በተመለከተ በፌደራል ደረጃ፣

- ለአሽከርካሪዎች አደጋን ተከላክሎ የማሽከርከር የስልጠና ማኑዋል ዝግጅት፣
  - ✓ ለህዝብ ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች፣
  - ✓ ለጭነት ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች፣
  - ✓ ለመንግስት ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች፣
- ለሐይማኖት አባቶች፣ ለጎሳ መሪዎችና ለሃገር ሽማግሌዎች የሚሆን የግንዛቤ ማስጨበጫና አደጋውን በምከላከሉ ዙሪያ ያለባቸውን ሀገራዊ ሃላፊነት የሚያስገነዝብ የስልጠና ማኑዋል ማዘጋጀት፣
- ለሴቶች፣ ለወጣቶች/አደረጃጀት/ እና ለአካለ ጉዳተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫና አደጋውን በመከላከሉ ስራ ላይ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የሚያስገነዝብ የስልጠና ማኑዋል ማዘጋጀት፣
- ለመምህራንና ለተማሪዎች የሚሆን የግንዛቤ ማስጨበጫና ተማሪዎችንም ሆነ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ከአደጋው ከመጠበቅ አኳያ የድርሻቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የሚያመላክት የስልጠና ማኑዋል ማዘጋጀት፣
- ለሚዲያ አካላት ፣ለኮሚኒኬተሮች፣ ለኪነጥበብ ባለሙያዎችና ለትራፊክ ተቆጣጣሪዎች የሚሆን የግንዛቤ ማስጨበጫና በሚሰሯቸ ተግባቦታዊ ሁነቶች ላይ የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ከማስፈን አኳያ እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል ማኑዋል ማዘጋጀት፣

- ለከተማና ለክልል ትራፊክ ፖሊሶች፤የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ባለሙያዎች የሚሆን የስልጠና ማኑዋል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ማዘጋጀት

*ክልሎች በፌደራል ደረጃ በሚዘጋጀው የስልጠና ሰነድ ላይ የክልላቸውን ነባራዊ ሁኔታ ተጨማሪ በማድረግ የስልጠና ሰነዱን አዳብረው ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ወይም የራሳቸውን ሊያዘጋጁ ይችላሉ።*

## 7.5. የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት

በዓሉ ከሚከበርበት ቀን በፊት የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ከማስፈን አኳያ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ ተብለው ለሚታሰቡ አካላት በክልል፤በወረዳና በዞን በፊት ለፊት ገለፃና ማብራሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን ስልጠና የሚሰጣቸውም አካላትም:–

- ለከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች *ብዛት*
- ለመለስተኛና አነስተኛ የከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች ባጃጅና ሞተርን ጨምሮ ..........
- ለከተማ የጭነት ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች ..........
- ለመንግስት ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች ..........
- ለሐይማኖት አባቶች፤ የጎሳ መሪዎችና የሃገር ሽማግሌዎች ..........
- ለሴቶችና የወጣቶች አደረጃጀቶች እንዲሁም ለአካል ጉዳተኞች ..........
- መምህራንና የተማሪ ትራፊክ ፖሊሶች ..........
- ለመንግስት ተቋማት ኮሚኒኬተሮችና የሚዲያ አካላት .........

➢ ለክልሉ ትራፊክ ፖሊሶች፤የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ባለሙያዎች ስልጠና የሚሰጥ ይሆናል .........

ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች እንደክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ የህትመት ዓይነታቸውንና የሰልጣኞቻቸውን ብዛት በመወሰን የቅድመ እቅድ ትግበራ ስራዎቻቸውን በሚያወጡት የማስፈፀሚያ እቅድ መሰረት ቀደም ብለው የሚያጠናቅቁ የሆናል።

## 7.6. መንገዶችን ለመንገድ ተጠቃሚዎች ምቹ የማደረግ ስራ

በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ተደጋጋሚ አደጋ የሚበዛባቸውንና ሌሎች ለመንገድ ተጠቃሚዎች ምቹ ያለሆኑ መንገዶችን በመለየት የተለያዩ የፍጠነት መቀነሻ ስልቶችን የመቀየስ፤

መንገዶችን ተነባቢ ለማደረግ የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን የማጠናቀቅ እና በሂደትም ተግባሪያዊ የማደረግ ስራን ማከናውን ።

## 7.7. የትራፊክ ህጎች ትግበራ ላይ ቁጥጥር ማድረግ

በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ለትራፊክ አደጋ መከሰት ዋና ዋና ምክንያት በሆኑ አልኮልና አደንዛዥ ዕፅ ተጠቅሞ ከማሽከርከር በህግ ከተወሰነ ፍጥነት በላይ ማሽከርከርና በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ በአልኮል ቴስተርና በራዳር የታገዘ ጥብቅ ቁጥጥር በማደረግ በንቅናቄ ፕሮግራሙ የትራፊክ ህጎች ትግበራን የማረጋገጥ ስራ ይሰራል።

## 7.8. የአሽከርካሪ ብቃት ህጋዊነትን የማረጋገጥ ስራን ማከናወን

በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ደብተር ሳይኖራቸውና በህገወጥ የአሽከርካሪ ብቃት በሚያሽከርክሩ አሽከርካሪዎች ላይ የተጠናከረ የስራ ላይ ፍተሻ በማደረግ የማጥራት ስራን መስራት።

በተለይም የህዝብ የንግድ ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ደብተራቸውን በግልፅና በጉልህ በሚታይ መልኩ ከለር ኮፒ በማደረግ በጋቢና ውስጥ እንዲያንጠለጥሉ ይደረጋል።

## 7.9 የጥያቄና መልስ ውድድር ማካሄድ

የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ የሚችሉ በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ላይ የሚያተኩሩ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ የጥያቄና መልሰ ውድድሮችን ማካሄድ፣

## 7.10 የፓናል ውይይት ማካሄድ

የመንገድ ትራፊክ ደህንነትን ከማስፈን አኳያ ባሉ ውስንነቶችና ሊሰሩ በሚገባቸው ነጥቦች ዙሪያ ጉዳዩ በቅርበት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በተመረጠ ሚዲያ የፓናል ውይይት ማካሄድ፤

# 8. የንቅናቄ ፕሮግራሙ በየደረጃው የሚተገበርበት የአፈፃፀም አቅጣጫ፣

የህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች እስከታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ በሆነ መልኩ በበላይ ኃላፊዎች እየተመራ ማለትም፡–

- ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት አቅጣጫ መሰረት የፓርላማ አባላት በንቅናቄው ጉልህ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል፤
- በክልሉ ውስጥ ያሉ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ካውንስል አደረጃጀቶችን የንቅናቄ ፕሮግራሙ ባለቤት በማድረግ ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡
- በነ ፈቃደኞችንና ተማሪዎችን መልምሎ በማሰልጠን የህብረተሰቡን ተሳትፎና ንቅናቄውን እንዲያግዙ ማድረግ፤
- በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቋማት በመንገድ ደህንነት ዙሪያ የራሳቸውን እቅድ ቀርፀው ንቅናቄ ያካሂዳሉ
- በወረዳና በዞን ደረጃ፡-በወረዳውና በዞኑ የካቢኔ ስራ አሰፈፃሚ በበላይነት እየተመራ ተግባሪያዊ የሚደረገ ሲሆን፤
- በዞንና በወረዳ ደረጃ የመንገድ ታራፊክ ደህንነት ኮሚቴ የተዋቀ ከሆነ የዞንና የወረዳ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ኮሚቴና የካቢኔ ስራ አሰፈፃሚ በጣመራ ስራውን ይመሩታል፤
- በከተማ ደረጃ ፡- በከተማው ከንቲባና በከተማው የካቢኔ አባላት፣ የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊዎች ፕሮግራሙ ይመራል
- በክልል/በከተማ አስተዳደር/ ደረጃ በክልሉ ፕሬዚዳንት ወይም በከተማ አሰተዳደሩ ከንቲባ፣ በየደረጃው ባሉ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሮች፤ የትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊዎችና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ምክር ቤት አባላት እየተመራ እስከ ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ የሚከናወን ይሆናል፤ አፈፃፀሙም በየጊዜው ለብሔራዊ ኮሚቴው ሪፖርት ይላካል።

- የየከተማው ወይም የየክልሉ የትራንስፖርት ቢሮ/ባለስልጣን በየጊዜው ስራውን እየገመገመ ለፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን/አብይ ኮሚቴ/ ሪፖርት የሚያደርግ ይሆናል፡፡
- በአዲስ አበባ በፌደራል ደረጃ የሚካሄዱ የንቅናቄ ፕሮግራሞችን የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበርና ባለቤት በማደረግ በጋራ የሚተገብሩት ይሆናል፡፡
- የሀገራዊ ህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ የማጠቃለያ ፕሮግራም የግንቦት ወር የመጀመሪያው እሁድ 2009 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት አባላት፣ የክልልና የከተማ መስተዳድር ፕሬዚዳንቶችና ከንቲባዎች፣ የክልልና የከተማ መስተዳድር ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሮች፣ የትራንስፖርት ዘርፍ ኃላፊዎችና የፖሊስ ኮሚሽነሮች እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ኃላፊዎች በተገኙበት አዲስ አበባ በሚገኘው ሚሊኒየም አዳራሽ የሚከበር ሲሆን በእለቱም የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አደጋውን መቀነስ በሚያስችሉ ነጥቦች ዙሪያ የስራ አቅጣጫ ይሰጣሉ።

## 9. የንቅናቄ መደረኩ አተገባበር

ሀገራዊ የንቅናቄ የዘመቻ ፕሮግራሙ በሕብረተሰቡ ውስጥ ሰፊ ንቅናቄን መፍጠር እንዲያስችል ተደርጎ በሁለት መልኩ የተቀረፀ ሲሆን፤

- የመጀመሪያው ክፍለ የህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ ከሚጠቃለልበት 3 ቀናት በፊት በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች በተመረጡ ዋና ዋና መንገዶችና አደባባዮች ላይ በመሆን የመንገድ ትራፊክ አደጋ ተጎጂዎችና ቤተሰቦቻቸው የተለያዩ ዩኒፎርሞችን በመልበስ **"በትራፊክ አደጋ መጎዳት በኛ ይብቃ"** የሚል መልክት ከትራፊክ

ፖሊሶች ጋር በመሆን ያስተላልፋሉ።የመንገድ ተጠቃሚው ሁሉ በጉዞው ወቅት ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ የሚገልፅ ብሮሸርም ያሰራጫሉ።

- የህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ ከሚጠቃለልበት 3 ቀናት በፊት በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች **«አንድ ቀን በግሩ»** በሚል መርህ የእግር ጉዞ ይደረጋል፣
- በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች በተመረጡ ዋና ዋና መንገዶችና አደባባዮች ላይ በትራፊክ አደጋ የተጎዱ ተሽከርካሪዎች ከዓሉ ማጠቃለያ 3 ቀን በፊት በማስቀመጥ የመንገድ ተጠቃሚዎች ሁሉ የትራፊክ አደጋ አስከፊነትን በመረዳት የችግሩ የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ ይደረጋል።
- በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች በትራንስፖርት ቢሮዎችና ባለድርሻ አካላት አማካኝነት እስከታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ድረስ የዘለቀ ህዝባዊ ንቅናቄን ለመፍጠርና የባለቤትነት ስሜትን ለማስረፅ በርካታ ስልጠናዎች፣ ትምህርቶችና መልዕክቶች የሚተላለፍበትና በሕትምትም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች አማካኝነት ሠፊ የግንዛቤ ስራ የሚሠራበት ይሆናል፡፡ በዚህ ህዝባዊ የንቅናቄ ስራ የሀይማኖትና የጐሣ መሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣አካል ጉዳተኞች፣ መምህራንና ተማሪዎች፣ የሕዝብ፣የጭነትና የመንግስት ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎችና፣ እግረኞች የመንገድ ትራፊክ አደጋ ተጐጂዎች በአጠቃላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሁሉም የህብረተሠብ ክፍል ተሣታፊ ይሆንበታል፡፡ በመጨረሻም የየክልሉ ፕሬዝዳንቶችና የከተማ መስተዳድር ከንቲባዎች ለሚያስተዳድሩት የህብረተሰብ ክፍል በትራፊክ አደጋ እንዳይጎዳ መልክት የሚያስተላልፉበትና የስራ አቅጣጫ የሚሰጡበት ይሆናል።
    - በሁለተኛው ክፍል የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር በተገኙበት በሚሊኒየም አዳራሽ በርካታ ጥሪ የተደረገላቸው የፓርላማ አባላት፣ የክልል ፕሬዝዳንቶችና የከተማ መስተዳድር ከንቲባዎች፣ የፖለቲካ አመራሮች፣ የክልልና የከተማ ትራንስፖርት ኃላፊዎች፣ የፌደራልና የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነሮች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ

ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎች እና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት የመንገድ ትራፊክ አደጋ እየፈጠረ ያለውን ተፅዕኖ በተመለከተ የሚሳተፉበት፣ በአደጋው አሣሣቢነት ዙሪያ የሚመክሩበትና መፍትሄ የሚያመላክቱበት ሲሆን በመጨረሻም በጠቅላይ ሚኒስትሩና በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር አማካኝነት የስራ አቅጣጫ የሚሰጥ ይሆናል።

- ፕሮግራሙን ይበልጥ ለማድመቅና ህዝባዊ ንቅናቄውን ተደራሽ ለማድረግ በሚሊኒየም አዳራሽም ሆነ በተለያዩ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የንቅናቄ ፕሮግራሙ ሲካሄድ የአደጋውን አስከፊነት የሚያመለክቱ የፍቶ ግራፍ ኤግዚብሽንና የአሽከርካሪ ማሰለጠኛ ተቋማት የተሽከርካሪ መመርመሪያ ተቋማትና ሌሎችም ከትራንስፖርቱ ዘርፍ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተቋማት ሴክተሩን ለማዘመንና አደጋን ለመከላከል የሚያደርጓቸውን ጥረቶች የሚያሳይ አውደ ርዕይ የሚቀርቡ ሲሆን የችግሩን አሳሳቢነት የሚያጉሉ እውነታን መሰረት ያደረጉ ፊልሞች ይቀርባሉ፡፡
- ለሕብረተሰቡ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራም እየተካሄደ መሆኑን ለማስገንዘብም ሆነ ለመቀስቀስ እንዲቻል በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ዋና ዋና መንገዶችና አደባባዩች ላይ የማርሻል ባንድ የተለያዩ ጣዕም ዜማዎችን የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

## 10. የክልሉ/የከተማ መስተዳድሩ/ ህዝባዊ ንቅናቄ መድረክ የማጠቃለያ ፕሮግራም የሚተገበርበት አግባብ

- በክልል አቀፍ የማጠቃለያ ፕሮግራም ላይ የክልሉ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች፤ የካቢኔ አባላት፤ የወረዳና የዞን የስራ አስፈፃሚዎችና የመንግስት አደረጃጀቶች /ሴቶች፤

ወጣቶች/ የሀይማኖት አባቶች፤ የሀገር ሽማግሌዎች ታዋቂ ግለሰቦችና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት በክልሉ ፕሬዝዳንት /የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ/ አማካኝነት አደጋውን መቀነስ የሚያስችሉ የስራ አቅጣጫ በመስጠት የሚጠናቀቅ ይሆናል፣

- የኃይማኖት አባቶች ለምዕምናኑ በትራፊክ ደህንነት ዙሪያ መልክት ያስተላልፋሉ፣
- የትራፊክ አደጋ ተጎጂዎች አደጋው የሚያደርሰውን ቀውስ በተመለከተ መልክት ያስተላልፋሉ
- በማርሽ ባንድ የታገዘ በዓሉን የተመለከተ ቅስቀሳ በተመረጡ ቦታዎች ይካሄዳል፣
- የትራፊክ ፖሊስ በሞተር፣ በተሽከርካሪና በእግር የታገዘ ሰልፍ ያካሂዳል፣
- የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማትና የተሽከርካሪ መመርመሪያ ተቋማት አውደ ርዕይ ያቀረባሉ፣
- የትራንስፖርት ቢሮዎችና ሌሎችም አካላት የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን ለህዝብ ያቀርባሉ፡፡
- ከበዓሉ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሊሎችም ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

## 11. በፌደራል ደረጃ እቅዱን ተግባሪያዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ አደረጃጀት፤ተግባርና ኃላፊነት

### 11 .1 ብሔራዊ ኮሚቴ

የሀገራዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙን ስራዎች በበላይነት የሚመራ፣ የሚቆጣጠርና የሚገመግም አካል ሲሆን ወቅታዊ የስራ አቅጣጫዎችንም ይሰጣል፡፡

1. የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አቶ አህመድ ሼዴ የብሔራዊ ኮሚቴው የበላይ ጠባቂ፣

2. የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ አብዲሳ ያደታ የብሔራዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ፣
3. የትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ክቡር አቶ ካሳሁን ኃ/ማሪያም የብሔራዊ ኮሚቴው ፀሐፊ፣
4. የዘጠኙ ክልሎችና የሁለቱ የከተማ መስተዳድር ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊዎች የብሔራዊ ኮሚቴወ አባል፣
5. የመንገድ ፈንድ ፅ/ቤት ኃላፊ አባል፣
6. ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን አባል፣
7. የክልልና የከተማ አስተዳደር ፖሊሰ ኮሚሽን ኮሚሽነር አባል፣
8. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አባል፣
9. ትምህርት ሚኒስቴር አባል፣
10. የወጣቶች ፌዴሬሽን አባል፣
11. የኃይማኖት ተቋማት ህብረት አባል፣

## የብሔራዊ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ይህ ኮሚቴ በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ አብዲሳ ያደታ የሚመራ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሀገራዊ ንቅናቄ ፕሮግራም ዕቅድና በጀት ተቀረፆ እንዲቀረብ ለአብይ ኮሚቴው ትእዛዝ ይሰጣል።

- ተቀርፆ የሚቀርብለትን ፕሮፖዛል በመገምገም የታዩ ክፍተቶች እንዲሟሉ ግብዓት ይሰጣል መስተካከላቸውንም ይቆጣጠራል፣ ያፀድቃል ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል።
- በሀገር አቀፈ ደረጃ የንቅናቄ ፕሮግራሙ በሚፈለገው ልክ መሬት ላይ እንዲወርድና ህዝባዊ ንቅናቄ እንዲፈጠር ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች አቅጣጫ ይሰጣል።
- የሀገር አቀፍ ንቅናቄ ፕሮግራሙን አፈፃፀም በየወሩ ይገመግማል፤አቅጣጫ ይሰጣል።
- የንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተገኙበት እነዲከናወንና ቀጣይ የስራ አቅጣጫ እንዲሰጡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል።
- የንቅናቄ ፕሮግራሙን በተመለከተ ከከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎቸ ጋር የመረጃ ልወውጥ ያደርጋል።
- በንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ ላይ ለሚሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና የፖለቲካ አመራሮች ጥሪ ያስተላልፋል።
- ከፕሮግራሙ መጠናቀቅ በኃላ በአብይ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ጥቅል ሪፖርት ገምግሞ ያፀድቃል፤ተሞክሮዎች እንዲቀመሩ ያደርጋል።

## 11.2 አብይ ኮሚቴ

አብይ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ኮሚቴው ሆኖ የሚከተሉትን አባላትን ያካትታል፡፡

1. የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር..........................ሰበሳቢ
2. የአዲስ አበባ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ............................ ም/ሰብሳቢ
3. የአዲስ አበባ መንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ........ ................ ፀሀፊ
4. የፌ/ት/ባ የመ/ት/ደ/ት/ግንዛቤ ዳ/ዳይሬክተር ..................... ............. አባል
5. የብሄራዊ የመንገድ ደህንነተ ካውንስል ኃላፊ/ተወካይ ..................... አባል
6. የፌ/ፖ/ኮሚሽን .................................................................... አባል
7. አዲሰአበባ ፖሊስ ኮሚሽን........................................................ አባል

8. ተሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ማህበር........................................ አባል
9. የአ.አ መስተዳድር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ባለስለጣን ዋና ዳይሬክተር.. አባል
10. የህዝበ ትራንስፖርት የህዝብ ክንፍ ሰበሳቢ................................... አባል
11. የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ማህበር.............................................አባል
12. የጭነት ትራንስፖርት የህዝበ ክንፍ ሰብሳቢ......................................አባል
13. የኢትዮጵያ ከባድ መኪና አሽከርካሪዎች ማህበር...............................አባል
14. የሀገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት ሾፌሮቸ ማህበር.........................አባል
15. የአዲስ አበባ ታክሲ ማህበር ህብረት...............................................አባል
16. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን.......................................................አባል
17. የፌ/ት/ባ/ ፋይናንስና ግዥ ዳ/ዳየሬክተር............................................አባል
18. የፌ/ት/ባ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት..........................አባል
19. የኢትዮጵያ የክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝ.......................................አባል

## የአብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ይህ ኮሚቴ በትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራትን ያከናውናል፡፡

- ንዑሳን ኮሚቴዎችን ያደራጃል፣ያሰማራል፣ ይከታተላል።
- ከብሔራዊ ኮሚቴው እቅድ በመነሳት የስራውን ዝርዝር ተግባር እቅድ በመንደፍ ለንዑስ ኮሚቴው ያስተዋውቃል ተግባራቱንም ለንዑስ ኮሚቴው እንደ አግባቡ ያከፋፍላል፣
- የተግባርና የበጀት አፈፃፀምን ይከታተላል፤ ይገመግማል።

- በሂደት የገጠሙ ችግሮችን እየለየ ውሳኔ ይሰጣል፤ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን በመለየት ለብሔራዊ ኮሚቴው አቅርቦ ያስወስናል።
- የንዑስ ኮሚቴዎችን ሪፖርት እየተቀበለ በየአስራ አምስት ቀኑ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል አቅጣጫ ያስይዛል፣
- ከንዑስ ኮሚቴ አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችን መፍትሄ ይሰጣል፣
- የንቅናቄ ፕሮግራሙን ሂደት አፈፃፀም በየወሩ ለብሄራዊ ኮሚቴው ያቀርባል፤ አቅጣጫዎችንም ይቀበላል፡፡
- በክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች እየተከናወኑ ያሉ የንቅናቄ ፕሮግራሞችን ሂደት ይከታተላል።

***በክልል/በከተማ አስተዳደር/ ደረጃ የሚደራጁ ኮሚቴዎች***

### 11.3 የክልሉ /የከተማው/ አብይ ኮሚቴ

የክልሉ/ የከተማ አስተዳደሩ/ አብይ ኮሚቴ፡- ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ኮሚቴው ሆኖ ክልል አቀፍ የንቅናቄ ፕሮግራሙን በበላይነት የሚመራ፤የሚቆጣጠርና የሚገመግም አካል ሲሆን ወቅታዊ የስራ አቅጣጫዎችንም እንዲሰጥ ሃላፊነት ኖሮት የሚዋቀር ይሆናል። በዚህም መሰረት የሚከተለውን አደረጃጀት መሰረት አድርጎ ቢቋቋም ይመረጣል

**አብይ ኮሚቴው የሚከተሉትን አባላት ያካትታል፡፡**

1. የክልሉ ፕሬዝዳንት /ከንቲባ/............................................የበላይ ጠባቂ
2. የክልሉ ትራንስፖርት ቢሮ ዋና ዳይሬክተር...................................ሰበሳቢ
3. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ም/ሰብሳቢ...................................ም/ሰብሳቢ

4. የክልሉ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ካውንስል ……………………………ፀሀፊ

5. የገጠር መንገዶች ባለስልጣን………………………………………………አባል

6. የክልሉ ተሽከርካሪ ማሰልጠኛ ተቋማት ማህበር ተወካይ…………………አባል

7. የክልሉ የተሽከርካሪ መመርመሪያ ተቋማት ተወካይ………………………አባል

8. የክልሉ የህዝበ ትራንስፖርት የህዝብ ክንፍ ሰበሳቢ………………………..አባል

9. የፌ/ት/ባ/ ፋይናንስና ግዥ ዳ/ዳየሬክተር…………………………………..አባል

10. የክልሉ የህዝብ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት……………………....አባል

እና ሌሎችንም አካላት አካቶ የሚዋቀር ይሆናል

**የክልሉ አብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

ይህ ኮሚቴ በትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራትን ያከናውናል፡፡

- ከብሔራዊ ኮሚቴው እቅድ በመነሳት የስራውን ዝርዝር ተግባር እቅድ በመንደፍ ለንዑስ ኮሚቴው ያስተዋውቃል ተግባራቱንም ለንዑስ ኮሚቴው እንደ አግባቡ ያከፋፍላል፣
- በክልል ደረጃ የንቅናቄ ፕሮግራሙ በሚፈለገው ልክ መሬት ላይ እንዲወርድና ህዝባዊ ንቅናቄ እንዲፈጠረ ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች አቅጣጫ ይሰጣል።
- የንቅናቄ ፕሮግራሙን በተመለከተ ከከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች ጋር የመረጃ ልወውጥ ያደርጋል።
- በንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ ላይ ለሚሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና ለፖለቲካ አመራሮች ጥሪ ያስተላልፋል።

5. የክለሉ የሚዲያ ተቋማት..........................................................አባል

6. የክለሉ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የስራ ሂደት ኃላፊ/ተወካይ .........አባል

7. እንዲሁም ለስራው አጋዥ የሆኑ ሌሎችንም አካላት አካቶ ቢዋቀር ይመከራል፡፡

**ተግባርና ኃላፊነት**

- እቅዱን በዝርዝር አዘጋጅቶ ለአብይ ኮሚቴው በማቅረብ ያፀድቃል፣
- ለፕሮግራሙ የሚመረጡ ቦታዎችን ያመቻቻል፣
- ለፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን የጥሪ ደብዳቤ ያስተላልፋል፣
- የተመረጡ ቦታዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ዲኮሬት ያደርጋል፣
- በፕሮግራሞች ላይ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በሙሉ ያሟላል፣
- ጥሪ የተደረገላቸውን እንግዶች ቦታ እንዲይዙ ያደርጋል፣
- በመስተንግዶ ሰአት የመስተንግዶ ስራ ይሰራል፣አዳራሽ ያዘጋጃል፣
- የተዘጋጁ የፕሮሞሽን ማቴሪያሎች ያሰራጫል፣
- አጠቃላይ የሚዲያና የኮሚኒኬሽን ስራዎችን በህትመት፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በማህበራዊ ድረገፅና በኤስ ኤም ኤስ በመታገዝ መረጃዎችን ይሰራጫል
- ፕሮግራሙ በፖሊስና መከላከያ እንዲሁም በረዳት የተማሪ ትራፊክ ፖሊስ፣ በተማሪዎች፣ሲቶችና ህፃናት ብሎም በትራፊክ ፖሊስ ሞተረኛ ሰልፍ እንዲታጀብ ያደርጋል፣
- የመድረክ መሪ እንደአሰፈላጊነቱ መመደብ ወይም ሌላ አማራጭ በመጠቀም ማዘጋጀት፣
- ከክልሉ ፖሊስ የማርሽ ባንድ ጋር በመነጋገር ፕሮግራሙ ድምቀት እንዲኖረው ያደርጋል፣

- የተጋፊጩ ተሽከርካሪዎችን በዋና ዋና መንገዶች ላይ እንዲቀመጡና በወቅቱ እንዲነሱ ማደረግ፣
- አባላቱ በየሳምንቱ በመሰብሰብ የዕቅዱን አፈፃፀም ይገመግማሉ፣
- የአፈፃፀም ሪፖርቱን በየ 15 ቀኑ ለአብይ ኮሚቴው ያቀርባል፣
- ሌሎች ለፕሮግራሙ አስፈላጊ የሆኑ የኮምኒኬሽን ስራዎችን ይሰራሉ፣

***በፌደራል ደረጃ 19 አባላት ያሉት የህዝብ ግንኙነት የቅስቀሳና መስተንግዶ ንዑስ ኮሚቴ ( ሚዲያ) ተቋቁሟል፡፡***

### 11.4.2. የህትመትና ኤግዚብሽን አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ፣

- ይህ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለአብይ ኮሚቴው ሆኖ ለህትመት ስራና ለኤግዚቢሽን አውደ ርዕይ ቅርበት ያላቸውን ባለሙያዎች አካቶ ቢደራጅ የሚመረጥ ሲሆን የሚደራጀውም ንዑስ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባረና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

**ተግባርና ኃላፊነት**

- ዝርዝር ስራዎቹን በተመለከተ እቅድ ቀርፆ በማቀረብ በአብይ ኮሚቴው ያፀድቃል፤
- በአሉን የሚመለከቱ የፕሮሞሽን ማቴሪያሎችን
- (ብሮሸሮችን፣ ፖስተሮችን፣ ባነሮችን፣ ስቲከሮችንና ሌሎች የህትመት ሥራዎችን) ያዘጋጃል
- ለኤግዚብሽን የሚሆኑ ፎቶዎችን በመምረጥ ያሳጥባል፣ የፎቶ መግለጫ በማዘጋጀት ኤግዚብሽኑን ያቀርባል፣

- ለፕሮግራሙ ማጠቃለያ የሚሆን የትራፊክ ምልክት ያለበት እስክርብ ያዘጋጃል፤
- የአውቶሞቲቭ ኤግዚቢሽን እንዲካሄድ ያደርጋል፣
- በየሳምንቱ በመሰብሰብ የስራውን ሂደት ይገመግማል፣
- በየ15 ቀኑ ለአብይ ኮሚቴው የስራ ሪፖርት ያቀርባል፣

***በፌደራል ደረጃ 13 አባላት ያሉት የህትመትና ኤግዚብሽን አስተባባሪ ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሟል።***

### 11.4.3. የክልሉ የሎጂስትክና አቅርቦት ንዑስ ኮሚቴ

- ይህ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለአብይ ኮሚቴው ሆኖ በንቅናቄ ፕሮገራሙ ላይ የሎጂስቲክ ችግር እንዳይገጥም መፍትሄ ሊሰጡ በሚችሉ የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ስብጥር የሚደራጅ ሲሆን የሚዋቀረው ኮሚቴም የሚከተሉት የስራ ተግባራተና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

**ተግባራና ኃላፊነት**

- የስራ እቅደ አዘጋጅቶ ለአብይ ኮሚቴው በማቅረብ ያፀደቃል፣
- ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ያሟላል፣
- ግዥ ይፈፅማል፣
- የተሽከርካሪ አቅርቦት ምቹ ያደርጋል
- በየሳምንቱ በመሰብሰብ የስራ ሂደቱን እንቅሳሴ ይገመግማል፣
- በየ 15 ቀኑ የአፈፃፀም ሪፖርት ለአብይ ኮሚቴወ ያቀርባል፣
- ለፕሮግራሙ ድምቀት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ይፈፅማል፡፡

*በፌደራል ደረጃ 6 አባላት ያሉት የሎጂስትክና አቅርቦት ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሟል።*

11.4.4. የክልሉ የግንዛቤና ስልጠና ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ

- ይህ ንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለዓብይ ኮሚቴው ሆኖ የሚከተሉት ዓባላት ይኖሩታል፤

1. የክልሉ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት የስራ ሂደት መሪ............ሰብሳቢ
2. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ.......................................ም/ሰብሳቢ
3. የክልሉ አሽከርካሪ ብቃት የስራ ሂደት................................ፀሀፊ
4. ብሄራዊ መንገድ ደህንነት ካውንስል .................................አባል
5. ሌሎችንም የመንገድ ደህንነት ባለሙያዎችንና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ሂደቶችን አካቶ በአባልነት የሚደራጅ ይሆናል

ተግባራና ኃላፊነት

- ዝርዝር የስራ ዕቅድ በማውጣትና በአብይ ኮሚቴው ያፀድቃል፤
- የስልጠና ማኑዋል ማዘጋጀት፤
- የስልጠና የሚሆኑ ዶክመንተሪዎችን ማዘጋጀት፤
- ስልጠና የሚሰጣቸውን አካላት መለየት፤
- የስልጠና ቦታዎችን መለየት፤
- በተለያዩ ዘዴዎች ስልጠና ለሚሰጣቸው አካላት ጥሪ ማስተላለፍ፤
- ስልጠና የሚሰጡ አካላትን መለየት ወይም መስጠት፤
- ስልጠና ለወሰዱ አካላት የእውቅና ሰርተፊኬት መስጠት፤
- በየሳምንቱ በመሰብሰብ የስራ እንቅስቃሴውን ይገመግማል፤

- በየ 15 ቀኑ የትግበራ ሂደቱን የተመለከተ ሪፖርት ለንዑስ ኮሚቴው ያቀረባል፤
- በተመረጡ ቦታዎች ላይ የትራፊክ አደጋ ተጎጂዎች ከትራፊክ ፖሊስ ጋር በመቀናጀት መለክት እንዲያስተላልፉ ያደርጋል

***በፌደራል ደረጃ 11 አባላት ያሉት የግንዛቤና ስልጠና ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሟል።***

**11.4.5. ስፖንሰር አፈላላጊ ንዑስ ኮሚቴ**

ይህ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለአብይ ኮሚቴው ሆኖ ክልሉ በሚያካሂደው የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራም ላይ የበጀት እጥረት እንዳያጋጥመው እስፖንሰር በማፈላለገ ችግሩኙ አስቀድመው መፈታት በሚችሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባለሙያዎችና የስራ ኃላፊዎች የሚዋቀር ሲሆን የሚከተሉት የስራ ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል

**ተግባርና ኃላፊነት**

- የስራ እቅድ በማዘጋጀት ለአብይ ኮሚቴ በማቅረብ ያፀድቃል፣
- ለፕሮግራሙ መሳካት በጀት ያፈላልጋል፣
- በጀት የሚገኝባቸውን አማራጮች ይቀርጻል፣
- የተገኘውን በጀት በተቋሙ የአሰራር ስርአት መሰረት ገቢ ያደርጋል፣
- በየሳምንቱ እየተሰበሰበ የስራ ሂደቱን እንቅስቃሴ ይገመግማል፣
- በየ 15 ቀኑ የትግበራ ሂደቱን የተመለከተ ሪፖርት ለንዑስ ኮሚቴው ያቀረባል፣

***በፌደራል ደረጃ 9 አባላት ስፖንሰር አፈላላጊ ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሟል።***

### 11.4.6. ዶክመንተሪ ፊልም ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ

- ይህ ኮሚቴ በፌደራል ደረጃ ከሚዘጋጁ ዶክመንተሪ ፊልሞች በተጨማሪ እንደአስፈላጊነቱ ክልላዊ ለዛ ያላቸውን ዶክመንተሪዎችን ለመስራት ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካለሆኑ ድርጅቶች ስብጥር የሚደራጅ ሲሆን ኮሚቴውም የሚከተሉት የስራ ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

**ተግባርና ኃላፊነት**

- የስራ እቅድ በማዘጋጀት ለአብይ ኮሚቴ በማቅረብ ያፀድቃል፣
- ለዶክመንተሪ ዝግጀት የሚሆኑ ምስሎችን ይቀርፃል፣
- ለዶክመንተሪ ዝግጅት የሚሆኑ ቃለ-መጠይቆችን ያካሂዳል፣
- የዶክመንተሪ ዝግጅቱን እስክሪፕት ለአብይ ኮሚቴው አቅርቦ ያስገመግማል፣
- የዶክመንተሪ ዝግጅት የኤዲቲንግ ስራዎችን ይከታተላል፤የተጠናቀቀውንም ስራ ለዓብይ ኮሚቴው ያቀርባል፣
- በየሳምንቱ እየተሰበሰበ የስራ ሂደቱን እንቅስቃሴ ይገመግማል፣
- በየ 15 ቀኑ የትግበራ ሂደቱን የተመለከተ ሪፖርት ለንዑስ ኮሚቴው ያቀረባል፣

***በፌደራል ደረጃ 9 አባላት ያሉት ዶክመንተሪ ፊልም ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሟል።***

## 12. የንቅናቄ ፕሮግራሙ አተገባበር የክትትልና ድጋፍ አግባብ

- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ህዝባዊ ንቅናቄ ብሄራዊ ኮሚቴው በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ የእቅድ አፈፃፀሞችን በየወሩ እየተከታተለ ይገመግማል የስራ አቅጣጫዎችንም ይሰጣል ፤ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘውም ጊዜ የክትትልና የግምገማ ቀናትን በመቀየር ስራዎች በአግባቡ ስለመከናወናቸው በግምገማ ያረጋግጣል።
- የፌደራል ትራንስፖርት ባለሰልጣን/አብይ ኮሚቴው/ ሀገራዊ የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራም ሂደቱን በየ15 ቀኑ በአቅም ግንባታና የለውጥ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት እና በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ትምህርትና ግንዛቤ ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ህግ ትግበራ ዳይሬክቶሬት በኩል ከትራንስፖርት ቢሮዎች ሪፖርት በመቀበል እየመገምገም በየወሩ ለብሄራዊ ኮሚቴው ሪፖርት ያቀርባል።
- ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ክልል አቀፊ የሆኑ ህዝባዊ ንቀናቄ ፕሮግራሞችን በየሳምንቱ በመገምገምና አቅጣጫ በመስጠት ለፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባሉ ወይም ይልካሉ፤አሰፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የክትትልና የግምገማ ቀናትን በማሳጠር ስራዎቸ በአግባቡ ስለመከናወናቸወ ያረጋግጣሉ ።

## 13. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሀገራዊ የንቅናቄ ፕሮግራሙን በፌደራል ደረጃ ተግባሪያዊ ለማድረግ 2,086,612 በጀት የሚያስፈልግ ይሆናል

## 14. በእቅድ ትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች

- ለስራው ሊሰጥ የሚገባውን በቂ ትኩረት ያለመስጠትና የመንጠባጠብ እንዲሁም የባለቤትነት ስሜት መጓደል ችግር፣

- የተሽከርካሪ አቅርቦት እጥረት፣
- የበጀት እጥረት፣
- በስልጠና ላይ የሚካፈሉ አሽካሪዎች ፈቃደኝነት ማነስ፣

## 15. ሊወሰድ ሚገባው የመፍትሄ አቅጣጫ

- በንቅናቄ ፕሮገራሙ እቅድና ማኑዋሉ ዙሪያ በቂ ኦሬንቴሽን ሰጥቶ ወደስራ ማስገባት፤
- በተቻለ አቅም ለስራው ቅድሚያ ሰጥቶ ተሽከርካሪዎች እንዲመደቡ ማድረግ፤
- እስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶችን ማሳመን፤
- በተለያዩ መገናኛ ዞድዎች አማካኝነት ስለስልጠናው ጠቀሜታ አሽከርካሪዎችን ማሳወቅ፤

## 16.ማጠቃለያ፡-

1. የዝግጅት ጊዜ ከጥር 18 እስከ የካቲት 15/2009 ዓ.ም
2. የትግበራ ጊዜ ከየካቲት 16 እስከ ሚያዝያ 30/2009 ዓ.ም
3. የማጠቃለያ ጊዜ ግንቦት 6 ቀን 2009 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ ይሆናል።

## 17. በፌደራል ደረጃ በ2009 ዓ.ም የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ቀጣይነት ያለው ሀገራዊ ህዝባዊ ንቅናቄ ሰነድ

| ተራ ቁ. | የዝግጅቱ አይነት | የሚያከናውነው አካል | ለዝግጅቱ የሚያስፈልጉ ነገሮች | የሚከናወንበት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በህዝባዊው የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ንቅናቄ አላማና አተገባበር ዙሪያ የክልልና የከተማ ትራንስፖርት ቢሮ/ባለስልጣን ኃላፊዎችና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት በብሔራዊ ኮሚቴው ሰብሳቢ አማካኝነት ውይይት ይደረጋል | ➢ ብሔራዊና አብይ ኮሚቴ | ጥናታዊ ፅሁፎች፣የንቅናቄ ዘመቻው እቅድ ፓወር ፖይንት ዝግጅት | ጥር 18 እና 19 |
| 2 | በየደረጃው ያሉ የመ/ደ/ካውንስል አደረጃጀቶች የንቅናቄፕሮግራሙ ባለቤት በማድረግ ቀጣይነቱን የሚያረጋግጥ ግንዛቤ መፍጠር | ➢ በክልሎችና በከተማ መስተዳድር ደረጃ የሚቋቋሙ አብይ ኮሚቴ | -ጥናታዊ ፅሁፎች፣የንቅናቄ ዘመቻው እቅድ | የካቲት ወር የመጀመሪያ ሳምንት |
| 3 | በጎ ፈቃደኞችን/ተማሪዎችን /መልምሎ በማሰልጠን የንቅናቄ ፕሮግራሙ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል | ➢ በክልሎችና በከተማ መስተዳድር ደረጃ የሚቋቋሙ አብይ ኮሚቴ | የስልጠና ማኑዋል ዝግጅት ፓወር ፖይንት ዝግጅት | የካቲት ወር ሁለተኛው ሳምንት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 4 | በመንገድ ትራፊክ ደህንነት ዙሪያ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በተመረጠ የሚዲያ ተቋም ውስጥ የፓናል ዲስከሽን ማካሄድ | ➢ በብሄራዊ፤ በአብይ ኮሚቴና የቅስቀሳና ኮሚኒኬሽን ኮሚቴ<br>➢ በክልል ደረጃ በሚቋቋም አብይ ኮሚቴና የቅስቀሳና ኮሚኒኬሽን ኮሚቴ | ከተመረጡ የሚዲያ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የፓናል ዲስከሽኑ በሚዲያ አማካኝነት ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ | የካቲት ወር አራተኛው ሳምንት |
| 5 | በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የሚገኙ የመንግስ መ/ቤት ተቋማት በመንገድ ደህንነት ዙሪያ የራሳቸውን እቅድ ቀርፀው በተቋማቸው ውስጥ ንቅናቄ እንዲያካሂዱ ማድረግ | በክልሎችና በከተማ መስተዳድር ደረጃ የሚቋቋሙ አብይ ኮሚቴ የሚተገብረው ይሆናል | በብሄራዊ ኮሚቴው የበላይ ጠባቂ ፤በክልል ፕሬዚዳንቶች ወይም በከተማ ከንቲባዎች ሰርኩላር እንዲበተን በማደረግ | ከየካቲት 20-የካቲት 30 |
| 6 | በፌደራልመ ሆነ በክልል ደረጃ የንቅናቄ ፕሮግራሙ ከመካሄዱ በፊት የሚከናወኑ ተግባራት<br>➢ የህትመት ስራን ማከናወን<br>➢ የዶክመንተሪ ፊልም ዝግጅትን ማከናወን<br>➢ የስልጠና ማኑዋል ዝግጅትን ማጠናቀቅ | ➢ የህትመት ዝግጅት ኮሚቴ<br>➢ የዶክመንተሪ ዝግጅት ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና ዝግጅት ኮሚቴ | -የተለዩዩ ፅሁፎች፤ ሊያውትና ዲዛይን ፤<br>-የተለያዩ ምስሎች ቀረፃ፤ ቃለመጠይቅ፤ የእስክሪፕት ዝግጅትና ኤዲቲንግ<br>-ለስልጠና የሚሆኑ የተለያዩ ፅሁፎች | -ከጥር20-የካቲት 15<br>-ከጥር20-የካቲት 15<br>-ከጥር20-የካቲት 15 |
| 7 | በፌደራለ ደረጃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት<br>➢ ለከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎችና የፖለቲካ አመራሮች<br>➢ 10,000 ለሚሆኑ ሀገር | ➢ በሔራዊና አብይ ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና ኮሚቴ | -ጥናታዊ ፅሁፎች፣ የፓወር ፖይንት ዝግጅት<br>-የፓወር ፖይንት ዘግጅት | የሚያዚያ ወር የመጨረሻው ሳምንት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | አቋራጭ,መለስተኛና የከተማና የህዝብ ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች<br>➢ 2,000 ለሚሆኑ በኢትዮ ጅቡቲ ኮሪደር ላይ ለሚያሽከረክሩ የጭነት ትራንስፖርት አሽከርካሪዎች<br>➢ 2000 ለሚሆኑ የመንግስት ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች<br>➢ 100 ለሚሆኑ የሐይማኖት አባቶች፤ የሃገር ሽማግሌዎች<br>➢ 200 ለሚሆኑ የሴቶችና የወጣቶች አደረጃጀቶች እና አካል ጉዳተኞች<br>➢ 100 ለሚሆኑ መምህራንና የተማሪ ትራፊክ ፖሊሶች<br>➢ 100 ለሚሆኑ ኮሚኒኬተሮችና የኪነጥበብ ባለሙያዎች<br>➢ 200 ለሚሆኑ ለከተማና ለክልል ትራፊክ ፖሊሶች፤የመንገድ ትራፊክ ደህንነት | ➢ የስልጠና ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና የቅስቀሳና ኮሚኒኬንሽ ኮሚቴ<br>➢ የስልጠና ኮሚቴ | -የፓወር ፖይንት ዘግጅት<br>-የፓወር ፖይንት ዘግጅት<br>-የፓወር ፖይንት ዘግጅት<br>-የፓወር ፖይንት ዘግጅት<br>-የፓወር ፖይንት ዘግጅት<br>-የፓወር ፖይንት ዘግጅት<br>-የፓወር ፖይንት ዘግጅት | ሁሉም ስልጠናዎች የስልጠና ኮሚቴ በሚያወጣው ዝርዝር ማስፈፀሚያ እቅድ መሰረት ከጥር20-ሚያዚያ 30 የሚጠናቀቁ የሆናል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ባለሙያዎች ፤ለሴፍቲ ዩኒት አባላት ስልጠና መስጠት | | | |
| 8 | የትራፊክ ህጎች ትግበራ ላይ/የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ደብተር ሳይኖራቸው እና ሰሌዳ ሳይኖራቸው እንዲሁም አልኮልና አደንዛዥ ዕፅ ተጠቅመው በሚያሽከረከሩ አካላት ላይ በቴክኖሎጂ ያገዘ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ | ➢ የክልልና የከተማ መስተዳድር ትራፊክ ፖሊስና የትራንስፖርት ተቆጣጣሪዎች | በንቅናቄው ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር | ከየካቲተ 1- ግንቦት 7 /2009/ዓ.ም |
| 9 | መንገዶችን ለመንገድ ተጠቃሚዎች ምቹ ማድረግ | ➢ በፌደራል ደረጃ በብሄራዊ ኮሚቴወና በአብይ ኮሚቴ የሚተገበረር ሲሆን<br>➢ በክልሎችና በከተማ መስተዳድር ደረጃ ደግሞ አብይ ኮሚቴው የሚተገብረው ይሆናል | በንቅናቄው ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር | ከየካቲተ 1- ግንቦት 7 /2009/ዓ.ም |
| 10 | የፓርላማ አባላት የንቅናቄ ፕሮግራሙ ጉልህ ተሳታፊ እንዲሆኑ ግንዛቤ ማሰጨበጥ<br>በክልል ደረጃ የካቢኔ አባላት የንቅናቄው ጉልህ ተሳታፊ እንዲሆኑ ግንዛቤ ማሰጨበጥ | ➢ ብሔራዊና አብይ ኮሚቴ<br>➢ የክልሉ አብይ ኮሚቴ | -ጥናታዊ ፅሁፎች፤የንቅናቄ ዘመቻው እቅድ<br>ፓወር ፖይንት ዝግጅት | የካቲ 3/07/ዓ.ም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 11 | በፌደራል ደረጃ የህዝባዊ ንቅናቄ ፕሮግራሙ ከሚጠቃለልበት 3 ቀናት በፊት በሁሉም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች አንድ ቀን በግራ በሚል መርህ የእግር ጉዞ ይደረጋል | ➢ በክልሎችና በከተማ መስተዳድር ደረጃ የሚቋቋሙ ብሄራዊና አብይ ኮሚቴ የሚተገብረው ይሆናል<br>➢ የህዝብ ግንኙነት ፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ/ሚዲያ | የተለያዩ የሚዲያና ኪሚኒኬሽን ስራዎችን በመስራት ህብረተሰቡን የንቅናቄው ተሳታፊ /ተግባር/ ማደረገ | በፌደራል ደረጃ በአዲስ አበባ የግንቦት ወር የመጀመሪያው ሳምንት<br><br>በሌሎች ክልሎችና የከተማ መስተዳድር የሚያዚያ ወር የመጨረሻው ሳምንት |
| 12 | የመ/ት/አ/ ተጎጂዎችና ቤተሰቦቻቸው የተለያዩ ዩኒፎርሞችን በመልበስ **"በትራፊክ አደጋ መጎዳት በኛ ይብቃ"** የሚል መልክት ከትራፊክ ፖሊሶች ጋር በመሆን ማሰተላለፍሉ። | ➢ የህዝብ ግንኙነት ፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ<br>➢ የዶክመንተሪ ዝግጅት ኮሚቴ | -የትራፊክ አደጋ ተጎጂዎችን ከትራፊክ ፖሊሰ ጋር ማቀናጀት | የግንቦት ወር የመጀመሪያው ሳምንት |
| 13 | የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የመንገድ ትራፊክ ደህነነት የጥያቂና መልስ ውድድር 2 ጊዜ ማካሄደ | ➢ የህዝብ ግንኙነት ፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ | ከተመረጡ የሚዲያ አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር ተሳታፊዎችን መለየትና ማካሄደ | ከንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ ሁለት ሳምንት ጀምሮ |
| 14 | በተመረጡ ዋና ዋና መንገዶችና አደባባዮች ላይ በትራፊክ አደጋ የተጎዱ ተሽከርካሪዎች ከንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ 3 ቀን | ➢ የህዝብ ግንኙነት ፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ<br>➢ ፎቶ ኤግዚብሽንና የህትመት | ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነተ መፍጠረና የተጎዱ ተሽከረካሪዎቸ በተመረጡ | የግንቦት ወር የመጀመሪያው ሳምንት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በፊት በማስቀመጥ የመንገድ ተጠቃሚዎች ሁሉ የትራፊክ አደጋ አስከፊነትን በመረዳት የችግሩ የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ ማደረግ። | ዝግጅት ኮሚቴ<br>➢ የዶክመንተሪ ዝግጅት ኮሚቴ | ቦታዎቸ እንዲቀመጡና እንዲጠበቁ ማደረግ | |
| 15 | የንቅናቄ ፕሮግራሙን ሂደት በተመለከተ በህትምትም ሆነ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች አማካኝነት ሠፊ ሽፋን እንዲያገኝ ማደረግ | ➢ -የህዝብ ግንኙነት ፤የቅስቀሳና ስተንግዶ ኮሚቴ | የእለቱ መልእክት፣ ባጅ፣ ባነር፣ ስቲከር፣ ፖስተር፣ ብሮሸር፣ ፎቶዎች፣ ዲስፕሌይ ማድረጊያ ወረቀት፣ ኡሁ፣ ማርከር፣ ፕላስተር | ከጥር 19 ጀምሮ የንቅናቄ ፕሮግራሙ እስኪጠናቀቅ ድረስ |
| 16 | ➢ ከንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ 2 ቀናት በፊት ጀምሮ የፍቶ ግራፍ ኤግዚብሽንና ከትራንስፖርት ዘርፍ ጋር የተያያዘ አውደ ርዕይ ማካሄድ ፡፡ | ➢ ፎቶ ኤግዚብሽንና የህትመት ዝግጅት ኮሚቴ እና የህዝብ ግንኙነት፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ | የተለያዩ ፎቶዎች ሞንታርቦ አነስተኛ ደንኳን አቅርቦት፤ | የንግቦት ወር የመጀመሪያው ሳምንት |
| 17 | ➢ የንቅናቄ ፕሮግራሙ ማጠቃለያ እለት የማርሻል ባንድ የተለያዩ ጣዕም ዜማዎችን በተለያዩ አደባባዮች ላይ እንዲያቀርብ ማድረግ፡፡ | ➢ የህዝብግንኙነት፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ | ጉዳዩ ከሚመከተው አካል ጋር ግንኙነት መፍጠር የተሽከርካሪ አቅርቦት | የግንቦት ወር የመጀመሪያው እሁድ |
| 18 | ➢ ለመንግስት የስራ ኃላፊዎች፤ለፖለቲካ አመራሮች፤ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት | ➢ ብሔራዊ ኮሚቴ<br>➢ አብይ ኮሚቴ<br>➢ የህዝብ ግንኙነት፤የቅስቀሳና | ጥሪ የሚደረግላቸውን አካላት መለየት፤ጥሪ ማስተላለፍና ክትትል ማድረግ | ከሚያዚያ ወር የመጨረሻው ሳምንት ጀምሮ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የትራንስፖርት ዘርፍ ኮሚቴ አባላት ፤ለክልልና ለከተማ ትራንስፖርት ቢሮዎች፤ለክልልና የከተማ ፕሬዚዳንቶች፤ለሀይማኖት አባቶች፤እና ሌሎች እንግዶች ጥሪ ማስተላለፍ | መስተንግዶ ኮሚቴ | | |
| 18 | ➢ የትራፊክ ፖሊሶች በሞተር ሳይክል፤ በተሽከርካሪና በእግር ጉዞ የታገዘ የሰልፍ ትርዒት እንዲካሄዱ ማደረግ | ➢ አብይ ኮሚቴ<br>➢ የህዝብ ግንኙነት፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ | ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር | የግንቦት ወር የመጀመሪያው እሁድ |
| 19 | ➢ በሚሊኒየም አዳራሽ የሚካሄደውን የማጠቃለያ ፕሮግራም በተመለከተ ዝርዝር ፕሮግራም ማዘጋጀት | ➢ አብይ ኮሚቴ<br>➢ የህዝብ ግንኙነት፤የቅስቀሳና መስተንግዶ ኮሚቴ | ዝርዝር የድርጊት መረሃ ግብር ማዘጋጀት ለፕሮግራሙ አስፈላጊ ከሆኑ አካላት ጋር ግንኙነት መፍጠር | የሚያዚያ ወር በሙሉ |

ከክልሉ /የከተማ መስተዳድሮች / እንደክልላቸው /ከተማቸው /ተጨባጭ ሁኔታ ከሃገራዊ የድርጊት መረሃ-ግብር በመነሣት ዝርዝር የአፈፃፀም የድርጊት መረሃ-ግብር ያዘጋጃሉ፡፡